# የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ

የአርበኞች ግንቦት 7፣ ለአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 358 መጋቢት 12 2007 ገጽ 1


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

በአርበኞች ግንቦት 7 እምነት የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተባባሪና መመሪያ የሚጠብቅበት ጊዜ አልፏል። ህወሓት የዘረጋው የአፈና ሥርዓት የጠበቀ ትስስርና ቁጥጥር ያለው ድርጅት ማቆም እንዳይቻል አድርጓል። ስለሆነም ያለን አማራጭ በርካታ ያለዘወትር የበላይ አካል ትክክል ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር የሚችሉ ስብስቦችን በመላው የአገራችን ክፍሎች በአፋጣኝ ማደራጀት ነው። ይህንን ደግሞ ማድረግ ይቻላል።

ከአርበኞች ግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በጎንደር ከተማ አንድ የሚሊሺያ አዛዥ ተገደለ በርካታ ሰዎችም ታሰሩ

የአገር ዉስጥ ምንጮች እንደገለጹት የጎንደር ከተማ የሚሊያሻዎች ሃላፊ ኮማንደር መጋቢት 11 ቀን 2015 ዓም ቀበሌ 15 ወይም ፋሲለደስ ትምህርት ቤት አካባቢ ከምሽቱ 2 ሰአት አካባቢ ላይ ማንነታቸው ባልታወቁ ታጣቂዎች ተገድሏል። ገዳዮቹም መሳሪያውን ማርከው ከእነ ትጥቃቸው ወደ አርማጭሆ ጫካ መግባታቸው ታውቋል። የጸጥታ ዘርፍ ሃላፊው ግንባሩ አካባቢ በጥይት የተመታ ሲሆን ወዲያውኑ ህይወቱ አልፏል። ድርጊቱን ተከትሎ የጸጥታ ሃይሎች አከታትለው በመተኮሳቸው ህዝቡ ሁኔታውን ለማየት ወደ አደባባይ ሲወጣ ወደያውኑ መብራት እንዲጠፋ ተድርጓል። አዣዡ በህዝቡ ላይ የተለያዩ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ይፈጽም እንደነበር የከተማዋ ነዋሪዎች ተናግረዋል። የፌደራል ፖሊስ አባላት አሁንም በአካባቢው እያንዣበቡ መሆኑን የአይን ምስክሮች ገልጸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ሰሞኑን ታጣቂዎች ገብተዋል በሚል መንግስት ከፍተኛ ቁጥር ሰራዊት በአብርሃ ጅራ፣ አብድራፊና አጎራባች ከተሞች አሰማርቶ ፍተሻ እያካሄደ ሲሆን፣ የአካባቢው ባለስልጣናትም ሳይቀር ተቃዋሚዎችን ትደግፋላችሁ ተብለው ተይዘዋል። .... ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ወያኔ ስኳርና ዘይት የሚያከፋፍለዉ ከምርጫ ካርድ ጋር እያያዘው ነው

በተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩ ነዋሪዎች እንደገለጹት በመጪው ግንቦት ወር ምርጫ የምርጫ ካርድ ያልያዙ ሰዎች ስኳርና ዘይት እንደማያገኙ እንደተነገራቸው ለኢሳት ተናግረዋል። አንዳንድ ቀበሌዎች የምርጫ ካርድ ዘይትና ስኳር ለመሸጥ የምርጫ ካርድ አብረው የሚጠይቁ ሲሆን፣ ካርድ ላልወሰዱት እንዲወስዱ እየጠየቁ ነው። መራጮች የመምረጥም ሆነ ያለ መምረጥ መብት ቢኖራቸውም፣ ገዢው ፓርቲ ከስኳርና ዘይት ጋር ማያያዙ ተገቢ አለመሆኑን ነዋሪዎች አክለዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ኢህአዴግበ97 ምርጫ ከ193 በላይሰዎች መገደላቸውን አምኗል። የገዢው ፓርቲ ልሳን የሆነቸው አዲስ ራእይ መጽሄት በየካቲ- መጋቢት እትሟ ቀጣዩ ምርጫም ከሰጋት ነፃ አይደለምብላለች። ለመጀመሪያ ጊዜ 25 ፓርቲዎች በተሳተፉበት የ1984 መለስተኛ እና አካባቢያዊ ምርጫ ከአሜሪካ መንግስታዊ ካልሆነ ድርጅት ተወክሎ የነበረውን ኤድመንድ ኬለር የተባለውን ጥቁር አሜሪካዊ ለኦሮሞ ነፃ አውጭ ግንባር ወግነሃል በሚል በ24 ሰአት አገር ለቆ እንዲወጣ እርምጃ እንደወሰደበት ያትታል። በሶስተኛው አገራዊ ምርጫ የ193 ወገኖች ህይዎት ለህልፈት ተደርጓል የሚለው አዲስ ራዕይ፤ .... ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የድምጻችን ይሰማ ትግል አሁን ካለበት ደረጃ ወደሚቀጥለዉ ምዕራፍ እንደሚሸጋገር ተነገረ

ላለፉት ሦስት አመታት ድምጻችና ይሰማ በሚል መሪ ቃል ዙሪያ ተሰባስበዉ ለስብዓዊና ለእምነት መብታቸዉ ሲታገሉ የሰነበቱት የኢትዮጵያ እስልምና እምነት ተከታዮች ቀጣዩ ትግላቸዉን አንድ ደረጃ ወደ ላይ ከፍ እንደሚያደርጉት ገለጸ። ባለፉት ሶስት አመታት የኢትዮጵያን ሙስሊሞች በመወከል ድምጹ እንዲሰማለት ጠይቆ፣ መለስ የተነፈገው ድምጻችን ይሰማ አመራሮቹን ለማስፈታትና ጥያቄዎቹ እንዲመለሱለት ግፊት ለማድረግ እስካሁን ሲከተለው ከነበረው የትግል ስልት አንድ ደረጃ ከፍ ያለ የትግል ስልት ይፋ እንደሚያድርግ አስታውቋል።ድምጻችን ይሰማ "መብቴን ካላከበርክ እኔም.." በሚል ርእስ ባወጣው መግለጫ፣ ህዝብ ሲመረው መብቴ ይከበርልኝ ከሚል ጩኸት መብቴን ካላከበርክ እኔም ወደ ሚል ዛቻ መሄዱ አይቀሬ ነው ብሎአል። ሙስሊሙ ኢትዮጵያዊ "መብቴን ካላከበርክማ" ወደሚል የትግል ምዕራፍ መሸጋገሩን የሚገልጸው ድምጻችን ይሰማ፣ ስለሚወሰዱ እርምጃዎች ዝርዝር መግለጫ ከመስጠት ተቆጥቧል። ይሁን እንጅ ሰሞኑን ስለሚወሰዱት እርምጃዎች መግለጫ እንደሚያወጣ አስታውቋል የሙስሊም የመፍትሄ አፈላላጊ የኮሚቴ አባላት አሁንም በፍትህ እጦት በእስር ቤት ውስጥ እየተሰቃዩ ይገኛሉ።

## አብርሃጅራ ከተማ በወያኔ የጸጥታ ኃይሎች ስትበረበር ሰነበተች

በአማራ ክልል ምእራብ አርማጭሆ ዉስጥ የምትገኘዩወ የአብርሃጅራሃ ከተማ ፀጉረ ልውጥ ሽፍቶችን ገብተዉባታል በሚል ከፍተኛ ፍተሻ በተባሉ ሰዎች ላይ ከፍተኛ ፍተሻ እየተደረገ መሆኑን ከአካባቢው አጋቢዎቻችን ከላኩልንና ከአካባቢዉ ከሚመጡ ዜናዎች ለማወቅ ተችሏል። የከተማው ሕዝብና የአካባቢው ገበሬ በከፍተኛ ሥጋት ላይ የሚገኙ ሲሆን፣ በሆቴሎች በዋና ዋና መንገዶችና መተላለፊያዎች ላይ ፍትሻ እየተካሄ ነው። ነዋሪዎች ደግሞ በሚሄዱበት አካባቢ ሁሉ መታወቂያቸውን እየተጠየቁ ነው። እስካሁን ድረስ በቁጥጥር ስር የዋለ አንድም ጸጉረ ልውጥ አለመኖሩን ነዋሪዎች አክለው ገልጸዋል። እየተደረገ ያለው ፍተሻ በከተማው ውስጥ የሚኖሩ ሁለት ታዋቂ ባለሃብቶች ከ3 ቀናት በፊት አርበኞች ግንቦት7ትን መቀላለቀላቸውን ተከትሎ የተደረገ ሳይሆን እንደማይቀር ይገመታል።

ካለፈው ወር ጀምሮ ወደ አካባቢው ለስራ የሄዱመተም ሆነ በአካባቢው የሚኖሩ ወጣቶች ወደ ኤርትራ በመሄድ ተቃዋሚዎችን ልተቀላቀሉ ትችላላችሁ እየተባሉ በመታፈስ ላይ መሆናቸውን የአካባቢው ምንጮች ተናግረዋል።

በአሁኑ ጊዜ በጠረፍ ከተማዎችና በሰሜን አርማጭሆ ከፍተኛ ውጥረት ያለ ሲሆን፣ ገዢው ፓርቲ ካለፈው ወር ጀምሮ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሰራዊቱን ወደ ስፍራው አንቀሳቅሷል።. ... ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## አቶ አብዲ ሙሃመድ አሜሪካ ዉስት ለደረሰባቸው ተቃውሞ ሃይለማርያም ደሳለኝን፣ ጌታቸው አሰፋንና ኢሳትን ወቀሱ

የሶማሊ ክልል ፕሬዚዳንት የሆኑት አቶ አብዲ መሀመድ ባለፈዉ ሰሞን ዋሺንግተን ዲሲ ዉስጥ ለደረሰባቸዉ ከፍነኝ ህዝባዊ ተቃዉሞ ዋነኛዉ ምክንያት ኢሳት የደህንነት ሹሙ ጌታቸዉ አሰፋና ተላላኪዉ ጠ/ሚ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ናቸዉ ሲሉ መወቀሳቸዉ ተሰማ።ዋሺንግተን ዉስጥ የደረሰባቸዉ ተቃዉሞ መክሸፉን የሚገልጹት ፕሬዚዳንት አብዲ፣ ኢሳት ቴሌቪዥንም ፕሬዚዳንቱ ሲናገሩት የነበረውን ንግግር ጥሩ ቢሆንም ሆን ብሎ እንዳይተላለፍ ያደረገው፣ እቅዱ መክሸፉን በመረዳቱ ነው ብለዋል።

ይህንን አስምልክቶ ኢሳት ቴሌቪዥን አስተያየቱን የጠየቀው በአንድ ወቅት የፕሬዚዳንት አብዲ የግል አማካሪ የነበረዉና የሶማሊ ክልል ወጣቶች ፕሬዚዳንት የነበረው፣ በአሁኑ ጊዜ በስዊድ አገር በስደት ላይ የሚገኘው ሰብአዊ መብት ተማጓቹ ወጣት አብዱላሂ ሁሴን ፣ አካራ ኒውስ በፈረንጆች አቆጣጠር በ2009 በፕሬዚዳንቱ ትእዛዝ መከፈቱንና እርሱ የውብሳይቱ ሃላፊና መስራች ሆኖ መስራቱን ገልጿል። ዌብሳይቱ ለልዩ ሚሊሺያ ከተመደበው የመንግስት በጀት ተቀንሶ መቋቋሙን የሚገልጸው አብዱላሂ፣ በዌብሳይቱ ላይ ለሚሰሩ ጋዜጠኞች ገንዘብ የሚከፈለውም ከክልሉ ባጀት መሆኑን ይናገራል።

አብዱላሂ ዌብሳይቱን ሲመራ በኦነበረበት ወቅት ያገኛቸውን ቁልፍ የቪዲዮ ማስረጃዎች በመያዝ ከአገር ከወጣ በሁዋላ፣ ዌብሳይቱ በፕሬዚዳንቱ ታናሽ ወንድም በከድር ሙሃመድ ኡመር ስም እንዲመዘገብ መደረጉን አስረድቷል። በውብሳይቱ ላይ የሚወጣውን ማንኛውንም ጽሁፍ በቃል እየተናገረ የሚያስጽፈው ፕሬዚዳንቱ መሆኑን አብዱላሂ ገልጿል። .... ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## ፊንጫ ስኳር ፋብሪካ ዉስጥ እሳት በሰዉና በንብረት ላይ አደጋ አደረሰ

በአገሪቱ ካሉና ስኳር በማምረት ላይ ከሚገኙት ወንጂና መተሐራ የስኳር ፋብሪካዎች በላይ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ፊንጫ ስኳር ፋብሪካ ላይ የተነሳው ድንገተኛ የእሳት ቃጠሎ በተለይ የፋብሪካው ሠራተኞች፣ አመራሮችና የአካባቢው ነዋሪዎች ባደረጉት ከፍተኛ ርብርብ ወደ ዋናው ፋብሪካ እንዳይዛመት ማድረጋቸውንና ሊተርፍ መቻሉን፣ የስኳር ኮርፖሬሽን ኮርፖሬት ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ዘመድኩን ተክሌ ተናግረዋል።

ባለፈው ቅዳሜ ከዋናው ፋብሪካ በቅርብ ርቀት ላይ በሚገኘውና ፋብሪካው ስኳር እንዲያመርት ኃይል የሚሰጠው የሸንኮራ አገዳ ጭማቂ ገለባ (ባጋስ) በእሳት መያያዙን የገለጹት ዳይሬክተሩ፣ ገለባውን በማቃጠል ወደ ኃይል እንዲለወጥ የሚያደርገው ባጋስ ማሽን ሙሉ በሙሉ በቃጠሎው ከመውደሙ በስተቀር፣ በፋብሪካው ዋና ዋና ክፍሎች ላይ ሳይዛመት መቆጣጠር መቻሉን አስታውቀዋል። የፋብሪካው ሠራተኞች .... ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## ተቀላቀሉን፤ ካልሆነም በያላችሁት ተደራጁ !

ህወሓት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ስለሚያደርሰው ዘርፈ ብዙ በደል ብዙ የተነገረለትና የተፃፈበት ብቻ ሳይሆን እየኖርንበት ያለ ሀቅ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብም የሚደርስበትን ስቃይ መታገስ ወደማይችልበት ጫፍ መድረሱ በሰበብ አስባቡ በሚፈነዳዱ ተቃውሞዎች የሚታይ ሀቅ ሆኗል።

በሌሎች አገሮች እንዲህ ዓይነት የሕዝብ ምሬት ሲኖር በጥቂት ግለሰቦችና ቡድኖች ጥሪ ሕዝብ ግልብጥ ብሎ አደባባይ ይወጣል። ከሕዝብ አብራክ የወጣው ጦር ሠራዊትና ፓሊስ ከተበደለው ሕዝብ ጎን በመቆም አምባገነኖችን አስወግዶ የሽግግር መንግሥት ያቆማል። በቅርብ ጊዜያት በሕዝባዊ እምቢተኝነት መንግሥት በተቀየረባቸው አገሮች ያየነው እንደዚህ ዓይነቱን ሀቅ ነዉ።

አገራችን ውስጥ ያለው ሁኔታ ግን ከዚህ በእጅጉ ይለያል። ህወሓት ኢትዮጵያ ውስጥ የገነባው የጦርና የፓሊስ ሠራዊት አመራር በዘር የተደራጀ በመሆኑ የሕዝቡን አጠቃላይ ብሶት ደግፎ ሊቆም ይችላል ብሎ መጠበቅ አይቻልም። ሠራዊቱ እንደ ተቋም  ከተበደለው ሕዝብ ጎን እንዲቆም በመጀመሪያ በራሱ በሠራዊቱ ውስጥ ሥር ነቀል ለውጥ መካሄድ አለበት። በዚህ አቅጣጫ የሚሠሩ ሥራዎች እንደተጠበቁ ሆነው፤ ሠራዊቱ ዘረኛ ገዢዎቹን አስወግዶ እስኪመጣ መጠበቅ አይቻልም፣ አይገባምም። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ፣ ሕዝባዊ እምቢተኝነት በሕዝባዊ አመጽ መታገዝ አለበት የሚለው ሁለገብ የትግል የትግል ስትራቴጂ ተመራጭ እንዲሆን ያደረገው ዋነኛ ምክንያት የሠራዊቱ ዘረኛ አወቃቀር ነው። በመረጥነው የትግል ስትራቴጂ መሠረት በሁለቱም ግንባሮች - ማለትም፣ በሕዝባዊ አመጽ እና በሕዝባዊ እምቢተኝነት ግንባሮች ሥራዎች መሠራት አለባቸው። ሁለገብ የትግል ስትራቴጂ እምንፈልገው ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ላይ እንዲያደርሰን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሁለቱም የትግል ስትራቴጂዎች አኳያ መደራጀት ይኖርበታል። ሕዝባዊ የአርበኛ ሠራዊት ማደራጀት እንደሚያስፈልግ ሁሉ በኢትዮጵያ ከተሞችና ገጠሮች፤ በሥራና በመኖሪያ አካባቢዎች በምስጢር የተደራጁ ሕዝባዊ የአርበኛ ሲቪል ክበቦችም በብዛት መደራጀት ይኖርባቸዋል።

በዚህም ምክንያት አርበኞች ግንቦት 7: የአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ ከህወሓት ዘረኛ ፋሽስታዊ አገዛዝ ነፃ ለመውጣት የሚመኝ ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንዲደራጅ ጥሪ ያቀርባል !  እያንዳንዱ ነፃነት ፈላጊ ኢትዮጵያዊ ከሚያምነውና ከሚመስለው ወዳጁ ጋር ይቧደን፤ ቡድኑንም በሥርዓትና በሚስጢር ያደራጅ።

ከእንግዲህ “ምን እንሥራ? ትግሉን እንዴት እንርዳ” እያሉ ለሚጠይቁ ወገኖቻችን በሙሉ መልሳችን “ከቻላችሁ ተቀላቀሉን፤ ካልሆነም በያላችሁት ተደራጁ” የሚል ነው። ድርጅት ኃይል ነው። መደራጀት በራሱ ትልቅ ሥራ ነው። ድርጅት ድርጅት የሚሆነው ደግሞ በሥርዓት ሲዋቀርና በሥነሥርዓት ሲመራ ነው። ስለሆነም ነፃነት ናፋቂ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሌላ አደራጅና አስተባባሪ እንዲመጣለት ሳይጠብቅ በራስ አነሳሽነት እንዲደራጅ ይህ ጥሪ ተላልፏል።
በሥርዓት የተደራጀ ስብስብ ሲኖር የሚሠራ ሞልቷል። ይህንን መንገርም አያስፈልግም። የተደራጀ ስብስብ ራሱ ሥራዎችን አቅዶ መሥራትም ይችላል። የሚከተሉት ነጥቦች ለአብነት ተዘርዝረዋል።

1. የተደራጀ ስብስብ ጠላትና ወዳጁን ይለያል። የጠላቱን ጥንካሬና ድክመቱን ከራሱ ጥንካሬና ድክመት ጋር መዝኖ የወገን ኃይልን ጥንካሬ የሚያጎለብቱ፤ ድክመቶቹን የሚቀንሱ እርምጃዎችን በመውሰድ አቅሙን ይገነባል።
2. የተደራጀ ስብስብ የጠላትን እንቅስቃሴ እየሰለለ መረጃ ለነፃነት ኃይሎች እንዲደርስ ያደርጋል።
3. የተደራጀ ስብስብ የተቀናጀ የሕዝባዊ እንቢተኝነት ተግባራትን ይፈጽማል። ለምሳሌ፣በሥርዓቱ የደረሰበትን ምሬት በወረቀት ገንዘብ፣ በአስፋልት፣ በታክሲዎችና በግድግዳዎች ላይ ይጽፋል፤ ገንዘቡን የኤፈርት ንብረት ከሆነው ውጋጋን ባንክ ያስወጣል፤ መዋጮዎችና ግብር ያጓትታል ከዚያም አልፎ አልከፍልም ይላል።
4. የተደራጀ ስብስብ በሥርዓቱ ላይ ለማመጽ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። ሁኔታች ተሟልተው አመጽ ሲቀሰቀስ ደግሞ ትግሉ ግቡን ሳይመታ እንዳይበርድ ፀንቶ ይቆማል።
5. የተደራጀ ስብስብ ወዳጆቹን አስተባብሮ በጥንካሬው ላይ ተመርኩዞ በአካባቢው ባለ የህወሓት ኃይል ላይ ክንዱን ያነሳል።

በአርበኞች ግንቦት 7  እምነት የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተባባሪና መመሪያ የሚጠብቅበት ጊዜ አልፏል። ህወሓት የዘረጋው የአፈና ሥርዓት የጠበቀ ትስስርና ቁጥጥር ያለው ድርጅት ማቆም እንዳይቻል አድርጓል። ስለሆነም ያለን አማራጭ በርካታ ያለዘወትር የበላይ አካል ትክክል ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር የሚችሉ ስብስቦችን በመላው የአገራችን ክፍሎች በአፋጣኝ ማደራጀት ነው። ይህንን ደግሞ ማድረግ ይቻላል።

ወቅቱ ህወሓትን ከጫንቃችን ላይ ለማውረድ የምንደራጅበት ነው። ድርጅት ኃይል ነው፤ አደራጅና አስተባባሪ ሳንጠብቅ በራስ ተነሳሽነት ዛሬውን እንደራጅ!

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!**

---

## በጎንደር ከተማ አንድ የሚሊሺያ አዛዥ ተገደለ ... ( ከገጽ 1 የዞረ )

በመተማ አካባቢ በቅርቡ ለመከላከያ ሰራዊት ደሞዝ ሊከፍሉ በመንገድ ላይ የነበሩ አንድ ኮሎኔል፣ አንድ መቶ አለቃ፣ አንድ ተራ ወታደርና ሹፎራቸው ተገድለው ገንዘቡ በታጣቂዎች ከተወሰደ በኋላ፣ ድርጊቱን የፈጸሙት ወደ አብርሃ ጅራ የገቡ የአርበኞች ግንቦት7 አባላት ናቸው በሚል ፍተሻ ሲካሄድ ሰንብቷል።

ምንጮች እንደሚሉት ታጣቂዎቹ 3 ክላሽንኮቭ ጠመንጃዎች፣3 ሽጉጦችንና 250 ሺ ብር የያዘ የገንዘብ መያዢያ ቀረጢት ይዘው ተሰውረዋል። ታጣቂዎቹ ምእራብ አርማጭሆ ገብተው ምሳ መብላታቸውን፣ የአካባቢውን ነዋሪዎች በሬ ግዝተው መጋበዛቸውንና ስለ አለማቸው ማስረዳታቸውን የሚገልጹት የአይን እማኞች፣ የአካባቢው ነዋሪም ድጋፉን እንደሰጣቸው ነዋሪዎች ተናግረዋል። በአብድራፊና አብርሃጅራ ከተማዎች  መምህራን፣ አንድ ሴቶች ጉዳይ ውስጥ በሃላፊነት የሚሰራ የመንግስት ሰራተኛ፣ የአካባቢው የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ሃላፊ፣ የመንግስት ታጣቂ ሚሊሺያ ተይዘው ታስረዋል። በአካባቢው የታሰሩት ሰዎች ቁጥር ከ20 በላይ መሆኑን ነዋሪዎች ይናገራሉ ወደኤርትራ በርሃ የሚሻገሩ ኢትዮጵያውን ቁጥር መበራከቱን ተከትሎ በሱዳንጠረፍዙሪያመከላከያሰራዊትየመውጫበር የተባሉትን ቦታዎች ሁሉ ዘግቶ ጥበቃውን አጠናክሯል። የአካባቢው ሰዎች እንደሚናገሩት ከተቃዋሚዎች ጋር ግንኙነት አላቸው በሚል በተለያዩ ወራቶች ከተገደሉት መካከል ዓስናቀውታፈረ፣  ሙሉጸሓይ፣ አቡሃይ ተክሌ፣ ፈንታ አዛናው ፣ ድግሴ አድየ፣ ታደሰ ድረስ፣ ተስፋው አለሙ፣ ሙሉጌታ ማሞ፣ ደጀን በይፋ፣ አለነ ተገኘ፣ ሙላው አለሙ፣ ጋራ ጉርባ፣ ተስፋ፣ ዳርጌ አወቀ፣ ደጉ፣ ጨምር፣ ጥላሁን፣ ሃብቴ አለምኔና ጸጋው ዘመነ የተባሉት ይገኙበታል። ምህረት አባይ የተባለው ባለስልጣን ደግሞ እነ ሙላው አለሙን ማስገደሉን ነዋሪዎች ሲናገሩ፣ ሹመት የሚባለው የጎንደር የጸጥታ ሹም ደግሞ ከሳንጃ እስር ቤት በማስወጣት በእነ ደጉ፣ ጨምርና ጥላሁን ላይ እርምጃ ወስዷል። በጉዳዩ ዙሪያ የወረዳዎችን አመራሮች  አስተያየት ለማካተት ያደረግነው ተደጋጋሚ ጥረት አልተሳካም።

---

## ወያኔ ስኳርና ዘይት የሚያከፋፍለዉ ከምርጫ ካርድ ... ( ከገጽ 1 የዞረ )

በከተማ ደረጃ ለደረሰው ውድቀት፤ የወጣቱን ተስፋ መቁረጥ፤ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን የምርጫ ስትራቴጅ – የአመፅ ሰልትና እና የቀለም አብዮት በምክንያትነት ጠቅሷል።

ተፎካካሪ እና ተቃዋሚ ፓርቲዎች በአንደኛ እና በሁለተኛው ምርጫዎች ከነባራቸው 12 ወንበሮች፣ በ1997ዓም 30 በመቶመቀመጫ ለማግኘት መቻላቸውን የሚያትተው መጽሄቱ፣ የአዲ ስአበባን ወንበር ከአንድበስተቀርሙሉ በሙሉ ማሸነፋቸውንም አትቷል። ከአፍሪካውያን በስተቀር ሌላ የውጭ አገር ታዛቢ አላስገባም የሚለው ኢህአዴግ፣ የውጭ ሃይሎች ስልጣን አስነጥቀው እስከመያዝ አቅም እንዳላቸው ያትታል። በአምስተኛው ምርጫ  አክራሪነት፤ ፅንፈኝነት፤  ተቃዋሚዎች በምርጫ የሚወስዱት አቋም ያሰጋናል ያለው ኢህአዴግ፣ የውጭታዛቢዎች ጉዳይ በህግ በመታገዱ ምክንያት የምንፈራውየውጭ ሃይሎች ተፅ ኖአይኖርም ሲል ከውጭ ስጋት ነጻ መሆኑን ገልጿል። አቶ ሃይለማርያም ደሳለኝ የአውሮፓ ህብረት ምርጫውን የማይታዘበው ባጋጠመው የገንዘብ እጥረት ምክንያት ነው ብለው ለፓርላማ  መናገራቸው ይታወሳል። የአውሮፓ ህብረት በበኩሉ ከዚህ ቀደም ያቀረብኩት የምርጫ ትዝብት ሪፖርት ተቀባይነት ባለማግኘቱ ቀጣዩን ምርጫ መታዘቡ ትርጉም እንደሌለው፣ ከመንግስት በኩልም ምርጫውን እንዲታዘብ ጥሪ እንዳልቀረበለት ተናግሯል። አዲስ ራእይ ከአፍሪካውያን በስተቀር የሌሎች አህጉሮች የምርጫ ታዛቢዎች እንዳያስታፉ ህግ መውጣቱን ቢናገርም ህጉ መቼና እንዴት እንደወጣ የሚታወቅ ነገር የለም።

# ህዳሴም ሆነ ዉዳሴ ከህዝብ የሚደበቅ ምንም ነገር የለም!

ከሰሞኑ አገራችን ኢትዮጵያን በተለይም ብሄራዊ ጥቅሟንና ደህንነቷን በተመለከተ ሁለት አቢይ ዜናዎች የአገራችን የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያ ጉዳዮች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸዉን አገሮች የአየር ሞገዶች ተቆጣጥረዉት ነበር። ከእነዚህ ዜናዎች ዉስጥ አንዱና ዋነኛዉ ኢትዮጵያ፤ ሱዳንና ግብፅ የህዳሴዉን ግድብ አስመልክቶ ስምምነት ላይ ደረሱ የሚል ዜና ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ አለም አቀፍ ጋዜጠኞች የህዳሴዉ ግድብ የሚሰራበት ቦታ ድረስ ሄደዉ ባካሄዱት ጥናት መሠረት የህዳሴዉ ግድብ ፕሮጀክት ባጋጠመዉ ከፍተኛ የገንዘብ እጥረት የተነሳ እንዲዘገይ መወሰኑን የሚያወሳ ዜና ነዉ። አርበኞች ግንቦት ሰባት ለአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ ኢትዮጵያ ዉስጥ ለሚሰሩ ምንም አይነት ስራዎችና በኢትዮጵያ ህዝብ ስም ከየትኛዉም አገር መንግስትና መንግስታዊ ካልሆነ ተቋም ጋር ለሚደረጉ ስምምነቶችና ዉሎች ሁሉ ባለቤቱ የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ነዉ ብሎ ያምናል፤ ስለሆነም አርበኞች ግንቦት ሰባት የኢትዮጵያን ህዝብ ብሄራዊ ጥቅምና ደህንነት ከሚመለከቱና በሚስጢር መጠበቅ አለባቸዉ ተብሎ ከሚታመኑ አንዳንድ ጉዳዮች ዉጭ ሌላ ምንም ስራ ወይም አለም አቀፍ ስምምነትና ዉል የኢትዮጵያ ህዝብ ሳያዉቀዉና ሳይሰማዉ በድብቅ መደረግ የለበትም የሚል የጸና እምነት አለዉ። ሆኖም ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉ አገዛዝ ኢትዮጵያን ከቅኝ ገዢዎች በከፋ መልኩ የሚገዛ የጥቁር ፋሺስቶች አገዛዝ በመሆኑ የሚሰራቸዉ ስራዎችና በአለም አቀፍ ደረጃ የሚፈርማቸዉ ዉሎችና ስምምነቶች የኢትዮጵያን ህዝብ ብሄራዊ ጥቅም የሚጻረሩና የሚጋፉ ድብቅ ስምምነቶች ናቸዉ።

ይህ የወያኔ መሪዎች ከኢትዮጵያ ህዝብ ጀርባ ላይ ተሸሽገዉ የሚሸርቡት የድብብቆሽ ሴራ ዛሬ የተጀመረ አዲስ ክስተት አይደለም። ባለራዕዩ መሪ የሚል አላስፈላጊ የቅጽል ስም የተሰጠዉ መለስ ዜናዊ በ2004 ዓም ሐምሌ ላይ ከዚህ አለም በሞት ሲለይ ዜናዉ ለኢትዮጵያ ህዝብ የተነገረዉ በነሃሴ ወር ማለቂያ ላይ ነበር እሱም ቢሆን ሞትን ያክል ነገር ደብቆ ማቆየት ስለማይቻል ነዉ እንጂ አይነግሩንም ነበር። ከዚህ በተጨማሪ በሰሜናዊዉ የአገራችን ክፍል ወያኔ ከጎረቤት አገር ጋር የተዋዋለዉ መሬት ቆርሶ የመስጠት ዉል የኢትዮጵያ ህዝብ ሳያዉቀዉና ሳይሰማዉ የተደረገ ዉል ወይም ስምምነት ነዉ።

አርበኞች ግንቦት ሰባት አገራችን ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝ ላይ ብቻ ሳይሆን ከግዛቷ ተነስተዉ ወደ ጎረቤት አገሮች በሚፈሱ አለም አቀፍ ወንዞቿና በሌሎችም የአገር ዉስጥ ወንዞቿ ላይ ግደብ የመስራት ማንም ሊጋፋዉ የማይገባ የተፈጥሮ መብት አላት ብሎ ያምናል። በሌላ በኩል ደግሞ አባይን በመሳሰሉ ድንበር ዘለል ወንዞች ላይ የሚሰሩ ምንም አይነት የልማት ፕሮጀክቶች በዛቻና በማንአለብኝነት ሳይሆን በመግባባት፤ በመመካከርና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶችን በሚያዳብሩ መልኩ መሰራት አለባቸዉ ብሎም ያምናል። አርበኞች ግንቦት ሰባት ይህንን የሚለዉ ደግሞ መሠረታዊ ኑሯቸዉ በአባይ ወንዝ ላይ አገሮች ሊያደርሱ የሚችሉትን የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ጫና በመፍራት ሳይሆን ትላልቅ የልማት ፕሮጀክቶች ከመጀመራቸዉ በፊት ፕሮጀክቶቹን አስመልክቶ ሊነሱ የሚችሉ ዋና ዋና ልዩነቶች መወገድ አለባቸዉ፤ ልዩነቶችን ለማስወገድ ደግሞ የተሻለና አዋጭ የሆነዉ አማራጭ ዲፕሎማሲ ነዉ የሚል ጽኑ እምነት ስላለን ብቻ ነዉ።

የወያኔ አገዛዝ እንደ ፈረንጆቹ ዘመን አቆጣጠር በ2011 ዓም የህዳሴዉን ግድብ ስራ ሲጀምር ከአራት ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ዶላር ወይም 96 ቢሊዮን ብር በላይ የተገመተዉ ግዙፍ ግድብ ስራ ሙሉ በሙሉ ከአገር ዉስጥ የገንዘብ ምንጮች በሚገኝ ገንዘብ እንደሚሰራና አገዛዙ ግድቡንና የግድቡን ስራ አስመልክቶ ምንም አይነት ድርድር ከማንም አገር ጋር እንደማያደርግ ለለህዝብ ቃል ገብቶ ነበር። የግድቡ ስራ በተጀመረ በጥቂት አመታት ዉስጥ የግድቡ ግንባታ የአገሪቱን የካፒታል ጥሪት ሙጢጥ አድርጎ በመብላቱና በሌሎች በተጀመሩና ሊጀመሩ በእቅድ በተያዙ የልማት ፕሮጀክቶች ላይ በግልጽ የሚታይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማድረግ በመጀመሩ አለም ባንክ፤ አለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅትና አያሌ ኢትዮጵያዉያን ምሁራን የግድቡ ስራና ግድቡ ላይ የሚፈሰዉ የካፒታል ብዛት እንደገና እንዲታሰብበት ምክር ለግሰዉ ነበር፤ ሆኖም ምክሩ የተሰጠዉ የሚሰማ ጆሮ ለሌለዉ ለወያኔ ነበርና ሰሚ ታጣ። ዛሬ ግድቡ ከተጀመረና ወያኔም በህዳሴዉ ግድብ ላይ ከምንም ከማንም አልደራደርም ካለ ከአራት አመታት በኋላ አንደኛ የግድቡ ፕሮጀክት ስራ በገንዘብ እጥረት የተነሳ እንዲዘገይ ተደርጓል፤ ሁለተኛ ወያኔ የህዳሴዉን ገድብ አስመልክቶ ከግብፅና ከሱዳን መንግስታት ጋር ስምምነት ላይ ደርሶ የፊታችን መጋቢት 14 ቀን ስምምነቱን ለመፈረም ጎንበስ ቀና እያለ ነዉ።

ለመሆኑ ይህ ወያኔ ከሱዳንና ከግብፅ ጋር የህዳሴዉን ግድብ አስመልክቶ የሚፈራረመዉ የስምምነት ዉሳኔ ይዘት ምንድነዉ? ዉሳኔዉ በሦስቱ አገር መሪዎች ፊርማ ከመፅደቁ በፊት ለምንድነዉ የዉሳኔዉ ባለቤት የሆነዉ የኢትዮጲያ ህዝብ እንዲያዉቀዉ ያልተደረገዉ? ባለፉት አራት አመታት ኢትዮጵያ ዉስጥ ምንም አይነት ገቢ ከሌላቸዉ ከተማሪዎችና ከአረጋዉያን ጀምሮ እስከ ቀን ሰራተኛዉ ድረስ ለህዳሴዉ ግድብ ግንባታ ገንዘብ አዋጣ ወይም ቦንድ ግዛ እየተባለ በሩ ያልተንኳኳ ኢትዮጵያዊ የለም። ታዲያ ይህ የኢትዮጵያ ህዝብ በራሱ ገንዘብ ለዕድገቴና ለብልፅግናዬ መሠረት ይሆነኛል ብሎ የሚያሰራዉ ግድብ ስራዉ በገንዘብ እጥረት ሲተጓጎልና በዚሁ ግድብ ዙሪያ ከዉጭ መንግስታት ጋር አለም አቀፍ ስምምነቶች ሲደረጉ ምንም የማይነገረዉ ለምንድነዉ?

የወያኔ መሪዎች ከሱዳንና ከግብጽ መሪዎች ጋር የህዳሴዉን ግድብ አስመልክቶ የተዋዋሉትን ዉል እንመራዋለን ብለዉ ከሚናገሩት ህዝብ ቢደብቁም ካርቱምና ካይሮ ወስጥ ሾልከዉ የወጡ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ግብፅ የህዳሴዉ ግደብ ፕሮጀክት ላይ የቁጥጥርና የማነጅመንት ድርሻ እንደሚኖራት እየተነገረ ነዉ።እንደዚህ አይነቶቹ ከዚህ ቀደም በፍጹም የማይሞከሩ ወይም የማይታሰቡ ናቸዉ ተብለዉ ሲነገሩ የነበሩ ስምምነቶችና ዉሎች ዛሬ ተደርገዉና የሶስትዮሽ ስምምነት ተደርሶባቸዉ በፊርማ የሚጸድቁት ግድቡን ሰርቶ ለመጨረስ የሚያስፈልግ ገንዘብ ለማግኘት ነዉ ወይስ ሌላ ድብቅ አላማ አለዉ? ደግሞስ ግድቡ የሚሰራዉ ለህዝብ ግድቡን የሚሰራዉም ህዝብ ሆኖ ሳለ ለምንድነዉ ይህ በዉድም በግድም ገንዘብ ካላዋጣህ ወይም ቦንድ ካልገዛህ እየተባለ ቀንና ማታ ሲጠየቅ የኖረ ህዝብ በዚህ ግድብ ዙሪያ የሚደረጉ ዉሎችንና ስምምነቶችን እንዳያዉቅና ጭራሽ እንዳይሰማ የተደረገዉ? ካይሮና ካርቱም ዉስጥ እንደሚነገረዉ ግብፅ በህዳሴዉ ግድብ ግንባታ ዙሪያ የማነጅመንትና የቁጥጥር ሚና ይኖራታል የተባለዉ ዜና እዉነት ከሆነ እኛ እራሳችን አገራችን ዉስጥ በምንሰራዉ ግድብ ግብፅ ሊኖራት የሚችለዉ የማነጅመንትና ቁጥጥር ድርሻ ዬት ድረስ ነዉ የሚሆነዉ ...ለምንስ እንዲህ አይነት ሚና እንዲኖራት ተደረገ?

አርበኞች ግንቦት ሰባት የሶስቱ አገሮ መሪዎች ስምምነቱን በፊርማ ከማጽደቃቸዉ በፊት የኢትዮጵያ ህዝብ ለእንደነዚህ አይነት ቁለፍ ጥያቄዎች መልስ ማግኘት አለበት ብሎ ያምናል። የኢትዮጵያ ህዝብ ኢትዮጵያን አስመልከቶ የሚደረጉ ምንም አይነት ዉሎችና ስምምነቶች ብቸኛዉ ባለቤት ነዉና ከዚህ ህዝብ ተደብቆ የሚደርግ ምንም አይነት ስምምነት ሊኖር አይገባም።ስለዚህም የኢትዮጵያ ህዝብ እነዚህ ከዚህ በላይ ያነሳናቸዉ ጥያቄዎች ጥርት ባለ መልኩ እንዲመለሱለት የወያኔን አገዛዝ ማስጨነቅ አለበት፤ አለዚያ ይህ ጉዳይ ዉሎ ካደረ በኋላ የሚደረገዉ ሩጫ ሁሉ “ቁጭ ብለዉ የሰቀሉትን ቆሞ ማዉረድ ያቅታል” እንደሚባለዉ ይሆናል።

ግብፅና ሱዳን የረጂም አመታት ወዳጅነትና አመታት ያስቆጠረ ወተዳራዊ ስምምነት ያላቸዉ ተጎራባች አገሮች ናቸዉ። እነዚህ ሁለት አገሮች በቅርቡ ከወያኔ ጋር የደረሱበትን ስምምነት “የግብፅን ፍላጎት የሚያረካ” ስምምነት ነዉ እያሉ ካርቱምና ካይሮ ዉስጥ አስተያየት በመስጠት ላይ ሲሆኑ ኢትዮጵያ ዉስጥ ግን ሁሉም ነገር ህዝብ እንዳያዉቀዉ በሚስጢር መያዙ እየታወቀ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤት “አዲስ ምዕራፍ” ተከፈተ እያለ የፈረደበትን የኢትዮጵያ ህዝብ መሸንገል ጀምሯል። በሌላ በኩል ደግሞ ወያኔ ሱዳንና ግብፅ በቅርቡ ካርቱም ላይ የደረሱበት ስምምነት እዚያዉ ካርቱም ዉስጥ የፊታችን ሰኞ በሦስቱ አገሮች መሪዎች ፊርማ ይጸድቃል ተብሎ በሚጠበቅበት በአሁኑ ወቅት የግብጹ ፕሬዚዳንት አብዱል ፈታ አል ሲሲ የዉጭ ጉዳይና የዉኃ ኃብት ልማት ሚኒስተራቸዉን አስጠርተዉ ሦስቱ አገሮች የደረሱበትን ሰነድ መርምረዉ ሪፖርት እንዲያቀርቡላቸዉ ማዘዛቸዉ ከወደ ካይሮ ተደምጧል። እንግዲህ ይታያችሁ እኛ ኢትዮጵያዉያን የሦስቱ አገሮች ስምምነት ምን እንደሆነ እንኳን ሳናዉቅ ግብፅ እሷ እራሷ የደረሰችበት ስምምነት አልጥም ብሏት ተጨማሪ ማብራሪያ እንዲሰጣት ጠይቃለች። ይህ የሚያሳየን አገሮች ለብሄራዊ ጥቅማቸዉና ደህንነታቸዉ ምን ያህል እንደሚጨነቁና አርቀዉ የሚመለከቱ አስተዋይ መሪዎች ደግሞ የሚጨንቃቸዉና የሚያሳስባቸዉ ይህ አሁን የሚመሩት ህዝብ ብቻ ሳይሆን ወደፊት በተከታታይ የሚመጣዉ ትዉልድ ጭምር መሆኑን ነዉ።እኛ ኢትዮጵያዉያን ግን ለእንደዚህ አይነት መሪዎች አልታደልንም። የኛ መሪዎች እንኳን ለሚመጣዉ ትዉልድ ሊጨነቁ ለዛሬዉም ትዉልድ “እኛ ከሞትን ሥርዶ አይበቀል” የሚሉ ስግብግቦች ናቸዉ።

ወያኔ ከራሱ ዉጭ ማንንም የማይሰማ፤ልዩነትን የማያስተናግድና የሌሎችን ሃሳብ ከሱ ሀሳብ የተሻለ መሆኑን እያወቀም ቢሆን የማይቀበል ችኮ መሆኑን በተደጋጋሚ አሳይቶናል። ዛሬ ላይ ቆመን ወደ ኋላ ዞር ብለን የትናንቱን ስንመለከት ወያኔ በህዳሴዉ ግድብ ዙሪያም ገና ከጥንስሱ ጀምሮ ያሳየን ይህንኑ ችኮነቱንና “እኔን ብቻ ስሙ” ባይነት ዕብሪቱን ነዉ። በተለይ የህዳሴዉን ግደብ በተመለከተ አባይ ወንዝ ላይ የሚገነባዉ ግድብ ከዚህ ቀደም በማንም ኢትዮጵያዊ ያልታሰበና የልተወጠነ ፍጹም አዲስ የሆነ ወያኔ ለኢትዮጵያ ያበረከተዉ ገጸ በረከት መሆኑን ለማሳየት ብዙ ጥሯል፤ አንዳንድ የዋሆችን ደግሞ አሳምኗል።ወያኔ ሁሌም ቢሆን ጥረቱና ፍላጎቱ እራሱን ከብጤዉ ከደርግ ጋር እያወዳደረ የተሻለ ሆኖ ለመታየት መሞከር ነዉ እንጂ የተሻለ ስራ መስራት ስላልሆነ በህዳሴዉ ግድብ ላይም አብዛኛዉን ግዜ ያጠፋዉ “አባይን የደፈረ” ተብሎ ለመጠራት ስለሆነ ዛሬ ግድቡ ግንባታዉ አልቆ አገልግሎት መስጠት በሚጀምርበት ወቅት የግድቡ ስራ ከመጀመሩ በፊት ተሰርተዉ ማለቅ

.... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## አህዴድ ጨለንቆ ዉስጥ የሰማዕታት ሐውልት አሰራ

ህወሓት ጦር ሜዳ ላይ የማረካቸዉን የቀድሞ የኢትዮጵያ ወታደሮች ሰብስቦ አዲስ አበባ ሊደርስ ሲል አምጦ የወለደዉ የኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦህዴድ) ለ25ኛ ኣመት የምስረታ በዓሉን ያሰራውን የሰማእታት ሃውልት ቅዳሜ መጋቢት 12 ቀን 2007 ዓ.ም በጨለንቆ ከተማ ያስመርቃል። ህወሃት እንደ ኦነግ ካሉ ድርጅቶች ጋር ግንባር ለመፍጠር የነበረው ፍላጎት ከከሸፈ በሃላ በ1982 ዓ.ም በሰሜን ሸዋ ደራ አካባቢ ጥቂት በምርኮ የተያዙ የቀድሞው ጦር ወታደሮችን በማሰባሰብ ህወሃት ድርጅት እንዲመሰረት ያደረገ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፣ አህዴድ በዚህ ታሪካዊ ቦታ 25ኛ ዓመት በዓሉን ሊያከብር ያልቻለው ከህወሃት ጋር የተሳሰረው ታሪኩ እንዲጎላ ባለመፈለጉ መሆኑን የኦህዴድ ምንጮች ጠቁመዋል። ኢሳት ባለፈው ሳምንት በአሉን በትግራይ ምድር ማክበር የሚለው ሃሳብ የህወሃት ባለስልጣናትን ይሁንታ አለማግኘቱን ዘግቦ ነበር። አህዴድ በትጥቅ ትግል ወቅት ህይወታቸውን የሰው ሰማዕታተ አጽም ከተለያዩ አካባቢዎች በማሰባሰብ በጨለንቆ በተሰራለት ሐውልት እንዲያርፍ የተደረገ ሲሆን፣ ይህንኑ ሐውልት ቅዳሜ ለመመረቅ ከፍተኛ የፌዴራልና የክልል ባለስልጣናት፣ የኦህዴድ አባላትና ከፍተኛ ካድሬዎች፣ አምባሳደሮች፣ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ድሬዳዋ ከተማ በመግባት ላይ ናቸው። 25ኛ የኦህዴድ የኢዮቤልዮ በዓል አከባበር ከጨለንቆ በተጨማሪ በነቀምቴ፣ በጅማ፣ በአምቦ፣ በሻሸመኔ፣ በአዳማ እና በፊኒፊኔ ከተሞች ከመጋቢት 9 እስከ 17/ 2007 ዓ.ም የተለያዩ ግንባታዎችን በመመረቅ፣ ሲምፖዚየም በማካሄድ በመከበር ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ የማጠቃለያ በዓሉ በአዲስአበባ ስታዲየም መጋቢት 17 ቀን እንደሚሆን ይጠበቃል።

በአቶ ኩማ ደመቅሳ፣ በአቶ አባዱላ ገመዳ፣ በጄኔራል ባጫ ደበሌና በሌሎችም በአጋጣሚ መመስረቱ የሚታወቀው አህዴድ፣ በምስረታ በአሉ ላይ ድርጅቱ ለነጻነታቸው ሲሉ የትጥቅ ትግል በጀመሩ ኦሮሞዎች እንደተመሰረተ ተደርጎ ሐሰተኛ ፕሮፖጋንዳ መሰራጨቱ አንዳንድ የህወሃት ነባር ታጋዮችን እንደላስደሰተ ታውቋል።

## አቶ አብዲ ሙሃመድ አሜሪካ ዉስት ለደረሰባቸው ተቃውሞ

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

አቶ አብዲ፣ የደህንነት ሹሙ አቶ ጌታቸው አሰፋና ጠ/ሚ ሃይለማርያም ደሳለኝ ተቃውሞውን አቀነባብረውታል ብሎ እንደሚያምን የገለጻው አብዱላሂ ምክንያቱ ደግሞ ከወራት በፊት ከተፈጠረው ክፍፍል ጋር ይያያዛል ብሎአል። የክልሉ የምክር ቤት አባላት 7 ለ5 በመወሰን አቶ አብዲን ከስልጣን ለማውረድ ሙከራ ቢያደርጉም፣ አቶ አብዲ ሀረር በሚገኙት በወዳጃቸው በጄኔራል አብራሃ አማካኝነት በስልጣን ላይ እንዲቆዩ መደረጉን አስታውሷል። 7ቱ የምክር ቤት አባላት አሁንም ተሰደው አዲስ አበባ እንደሚገኙ የሚገልጸው አብዱላሂ፣ በአቶ ሃይለማርያምና በአቶ ጌታቸው አሰፋ እንደሚደገፉም ገልጿል። አቶ አብዲ ለአቶ ሃይለማርያም ከፍተኛ ንቀት ያላቸው ሲሆን፣ ከእርሳቸው የሚመጣውን ትእዛዝ አይቀበሉም። አቶ አብዲ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ሰላም እንደሆኑ ለማሳየት ሁለቱ ሰዎች ጎን ለጎን ቁጭ ብለው የሚያሳይ ፎርጅድ ፎቶግራፍ አሰርተው በዚሁ ዌብሳይት ላይ እንዲወጣ ካደረጉ በሁዋላ፣ በደረሰባቸው ነቀፋ እንዲነሳ አድርገዋል።

በአቶ አብዲ ጉዳይ በአንድ በኩል የደህንነት ሹሙና አቶ ሃይለማርያም ደሳለኝ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የመከላከያው ሹም ጄኔራል አብርሃ ተፋጠው እንደሚገኙ የሚገልጸው አብዱላሂ፣ እስካሁን ባለው ሂደት መከላከያ በማሸነፉ እነ አቶ ሃይለማርያም ምንም ለማድረግ ሳይችሉ ቀርተዋል ብሎአል። ፕሬዚዳንቱ ወደ አገር ሲመለሱ ችግር አይገጥማቸውም ወይ ተብሎ ለተጠየቀው ሲመልስ ደግሞ፣ የመከላከያ ባለስልጣናት እጃው ውስጥ እስካሉ ድረስ ምንም እንደማይሆኑ ይናገራል። ነገሮች ገፍተው ከመጡም ውብሳይቱ የእኔ አይደለም ሊሉ እንደሚችል አክሏል። በመከላከያ አዛዦችና በአቶ አብዲ መካከል ያለው ግንኙነት ከግል ጥቅም ጋር የተሳሳረ መሆኑንም አብዱላሂ ይናገራል ። አቶ አብዲ ከኦብነግ ጋር የሚደረገው ድርድር ስልጣኔን አደጋ ውስጥ ይጥለዋል በሚል ስጋት አይቀበሉትም። የአካራ ኒውስ ውብሳይት መተዳዳደሪያ ጽሁፍ እንደሚያሳየው፣ ዌብሳይቱ ስለሶማሊ ክልል ወቅታዊ ሁኔታ ከባለስልጣኖች አንደበት የሚነገረውን እየተቀበለ እንደሚያሰራጭ ያትታል። በዌብሳይቱ ውስጥ የክልሉ ፕሬዚዳንት የሚያደርጉዋቸው እንቅስቃሴዎችና የአሜሪካ ጉብኝታቸው በፎቶ ተደግፎ ቀርቧል።በተመሳሳይ ዜና ደግሞ አቶ አብዲ በሚኒሶታ ከፍተኛ ተቃውሞ አጋጥሞቻዋል። በተቃውሞው ላይ የሶማሊ ተወላጆች ኢትዮጵአውያንና ሌሎች ኢትዮጵያውያን በአንድነት በመሆን አቶ አብዱላሂ እናቶችን የሚገድል፣ ጨፍጫፊ፣ ገዳይ የሚሉ የተቃውሞ ድምጾችን አሰምተዋል።

የሶማሊክልል ፕሬዚዳንት አብዲ ሙሃመድ ኡመር እና በክልሉ የካቢኔ አባሎች መካከል የተፈጠረውን ልዩነት ተከትሎ በጠ/ሚኒስትር ሃይለማርያም ደሳለኝ ጽ/ቤት በተካሄደው አስቸኳይ ግምገማ፣ ፕሬዚዳንቱ ፈጸሟቸው የተባሉ በርካታ ወንጀሎች ተዘርዝረው ቀርበዋል። ባለፈው ነሃሴ ወር አቶ ሃይለማርያም ደሳለኝ በሰብሳቢነት በመሩት ግምገማ ላይ ም/ል ጠ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን፣ የጠ/ሚኒስትሩ የጸጥታ ዘርፍ ሃላፊ አለቃ ጸጋየ በርሄ፣የደህንነት ምክትል ሹሙ ኢሳያስ ወጊዮርጊስ፣ የምስራቅ እዝ ዋና አዛዥ ጄኔራል አብርሃ በቅጽል ስማቸው ኳታር፣የፌደራልፖ ሊስወንጀል መከላከል ሃላፊ ጄ/ል ግርማ የመንጁስ፣ አቶ አዲሱ ለገሰ፣ አቶ አብዲ መሃመድና የተለያዩ የክልሉ የካቢኔ አባላት እንዲሁም ሌሎች 2 የኢህአዴግ ከፍተኛ አመራሮችም በተገኙበት አቶ አብዲ መገምገማቸውን ኢሳት ዘግቦ ነበር። አቶ አብዲ ስልጣን ከያዙ ጀምሮ እሳቸው በሚመሩት ሚሊሺያ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች መገደላቸውን፣ በርካታ ሲቪሎች ታስረው ህክምና ሳያገኙ በቀላፎ፣ በፌርፌርና በሌሎችም እስር ቤቶች እንዲሞቱ ማደረጋቸቸውን፣ ከመንግስት የተመደበውን ግዙፍ በጀት ለአንዳንድ የፌደራል ባለስልጣናት በተለይም ለጄ/ል አብርሃ ከ70 ሚሊዮን ብር በላይ በተለያዩ ወቅቶች እንዲሰጣቸው በማድረግና በተለያዩመንገዶች ከፍተኛ ገንዘብ እንዲዘርፍ ማድረጋቸው፣ የአገር ሽማግሌዎችን በመሰብሰብ በአንቀጽ 39 መሰረት የራሳችንን መንግስት ስለምናውጅ ለዚህ ታሪካዊ ክስተት ራሳችሁን አዘጋጁ፣ ፌደራል መንግስትም በውስጥ ጉዳያችን ጣልቃ መግባት አይችልም ብለው መናገራቸው፣ የልዩ ፖሊስ አባላትና የጎሳ አባላሎቻቸው ከፍተኛ ገንዘብ እንዲዘርፉ ማሰማራታቸው፣ በክልሉ የሚካሄዱትን ትላልቅ ፕሮጀክቶች ያለ ጫራታ በመስጠት ሆን ብለው ለብዝበዛ አዘጋጅተዋል የሚሉ የግምገማ ነጥቦች ቀርበውባቸው ነበር። በግምገማው ወቅት ጄ/ል አብርሃ በአቶ አብዲ ላይ የቀረበውን ግምገማ አጥብቀው መቃወማቸው ለአቶ አብዲ የስልጣን እድሜ መራዘም አስተዋጽኦ ማድረጉ በወቅቱ ተዘግቧል።

## አብርሃጅራ ከተማ በወያኔ የጸጥታ ኃይሎች

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

ይህ በእንዲህ እንዳለ ምእራብ አርማጭሆ ዉስጥ ዉጥረቱ አሁንም እንዳልበረደ ለማወቅ ተችሏል። በዚህም መሰረት ምእራብ አርማጭሆ ወረዳ በአብርሃ ጅራ ከተማ ተቃዋሚ ናቸው ተብለው የተጠረጠሩት ሁሉ እየተያዙ በመታሰር ላይ ናቸው። ካለፉት ሶስት ቀናት ጀምሮ እየተካሄደ ባለው ጥብቅ ፍተሻ በርካታ የኢህአዴግ አባላትና የጸጥታ ሃይሎች ተይዘው ሲታሰሩ፣ ቁጥራቸው በውል ያልተወቀ ነዋሪዎች ደግሞ አፈሳውን በመፍራት እያመለጡ የትጥቅ ትግል የሚያደርጉ ተቃዋሚዎችን በመቀላቀል ላይ ናቸው። እስካሁን በተደረገው አፈሳ የወረዳው ምክር ቤት የህዝብ ግንኙነት ዋና ሃላፊ ተቃዋሚዎችን ይረዳል በሚል ሲያዝ፣ ከ20 ያላነሱ የመንግስት ሰራተኞችና መምህራንም ተይዘዋል። ሁለት ፖሊሶች ደግሞ አምልጠው ተቃዋሚዎችን ተቀላቅለዋል። በአካባቢው ያለው አለመረጋጋት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ ሲሆን፣ ፌደራል ፖሊሶችና መከላከያ በህዝቡ ላይ ሽብር እየፈጠሩ መሆኑን ነዋሪዎች በመናገር ላይ ናቸው። በአብርሃጅራ የፋርማሲስት ባለቤት የሆኑትና በህዝቡ ዘንድ ከፍተኛ እውቅና ያላቸው አቶ አበራ ጀግኔ ድንበር አቋርጠው አርበኞች ግንቦት7ትን ተቀላቅለዋል ተብሎ መወራቱ የመንግስት የጸጥታ ሃይሎች አፈሳውንና ጥቃቱን እንዲያባብሱ እንዳደረጋቸው ነዋሪዎች ይገልጻሉ።

## ፊንጫ ስኳር ፋብሪካ ዉስጥ እሳት በሰዉና በንብረት

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

ለሕይወታቸው ሳይሳሱ ሠራተኞቹ ባደረጉት ርብርብ እሳቱን መቆጣጠር የተቻለ ቢሆንም፣ አቶ ተስፋዬ ለሚ የተባሉ የፋብሪካው ሠራተኛ ሕይወታቸው ማለፉን ዳይሬክተሩ ተናግረዋል። ከባድ ጉዳት የደረሰባቸው 11 ሠራተኞች በቤቴል ሆስፒታል ተኝተው እየታከሙ መሆኑንም አክለዋል። አምስት ሠራተኞችም የደረሰባቸው ጉዳት ቀላል ስለነበር በአካባቢው ክሊኒክ ሕክምና ተደርጎላቸዋል። ፋብሪካው ለጊዜው ሥራ ያቋረጠ መሆኑን የገለጹት አቶ ዘመድኩን፣ ምክንያቱ ደግሞ የኃይል ማመንጫ ማሽን በመቃጠሉ መሆኑንና እሱም ጥገናው ተጠናቅቆ በቀናት ውስጥ ሥራ እንደሚጀምር በእርግጠኝነት ተናግረዋል።

ፋብሪካው በቂ ክምችት ያለው መሆኑን የገለጹት አቶ ዘመድኩን፣ ከመጋቢት 5 ቀን 2007 ዓ.ም. ጀምሮ ላለፉት አራት ቀናት ፋብሪካው ሥራ ካቆመ በኋላ ለኅብረተሰቡ የሚደርሰው የስኳር ሥርጭት ሒደት እንዳይዛባ ከክምችት ወጥቶ እንደሚያከፋፈልም አስታውቀዋል። በፋብሪካው ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት ባለመድረሱ እንደተቃጠለ በማስመሰልና ምርት እንደሌለ የተሳሳተ መረጃ በመንገር የዋጋ ንረት እንዳይፈጠር ኅብረተሰቡ ሊያውቅ እንደሚገባና ጥንቃቄ

.... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

**የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz

አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz

በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz

በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## በሚስጢር የተያዘው የአባይ ግድብ ስምምነት ሊፈረም ነው

ግብጽ፣ ሱዳንና ኢትዮጵያ በሚስጢር ሲያደርጉት የቆዩት ድርድር ከተጠናቀቀ በሁዋላ፣ የሶስቱ አገር መሪዎች በተገኙበት በካርቱም እንደሚፈረም መረጃዎች አመልክተዋል። የፊርማ ስነስርአቱ የፊታችን ሰኞ በካርቱም የሚካሄድ ሲሆን፣ ዝርዝር ይዘቱ ለህዝብ ይፋ እንዳይሆን ተደርጓል። የአባይ ግድብ ከህዝብ በውዴታና በግዴታ በሚዋጣ ገንዘብ እየተገነባ መሆኑ እየታወቀ፣ ስምምነቱን ገንዘቡን ለሚያዋጣው ህዝብ ይፋ ለማድረግ ለምን እንዳልተፈለገ ግልጽ አይደለም። ሱዳንና ግብጽ ስምምነቱ የግብጽን ፍላጎት ያረካ ነው በማለት አስተያየት በመስጠት ላይ ሲሆኑ፣ የኢትዮጵያ መንግስት ግን በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አማካኝነት " አዲስ ምእራፍ" የከፈተ ከማለት ውጭ ለኢትዮጵያ ስለሚያስገኘው ጥቅም ምንም ያለው ነገር የለም።

## ህዳሴም ሆነ ዉዳሴ ከህዝብ የሚደበቅ

... ( ከገጽ 3 የዞረ )

የነበረባቸዉን ስራዎች እየሰራ ነዉ።

በቅርቡ አንድ አለም አቀፍ የጋዜጠኞች ቡድን ግድቡ የሚሰረባት ቦታ ድረስ በመሄድ የፕሮጀክቱን እንቅስቃሴ በተመለከተ ጥናት አትንቶ የግድቡ ስራ በከፍተኛ የገንዘብ እጥረት የተነሳ ይዘገያል ብሎ ሪፖርት ማቅረቡ የሚታወስ ነዉ። ጉዳዩን በቅርብ ለምናዉቀዉ ለኛ ለኢትዮጵያዉያን ግን እዉነቱ ከዚህ በላይ ነዉ። የህዳሴዉ ግደብ የሚዘገየዉ በገንዘብ እጥረት ብቻ አይደለም። የዚህ ትልቅ ፕሮጀክት ድህረ ጥናት ሁኔታዎችን የላጤነና ቅደም ተከተሎችን ያላገናዘበ ጎደሎ ጥናት ነበር፤ ከዚህ በተጨማሪ ሩጫዉና ግርግሩ የተጀመረዉ የህዳሴዉን ግደብ የመሰለ ግዙፍ የ96 ቢሊዮን ብር ፕሮጀክት በይድረስ ይድረስ ሰርቶ ለመጨረስ ነበር።

የብዙ አለም አቀፍና የአገር ዉስጥ ኤክስፐርቶች ግምት በግልጽ እንደሚጠቀመዉ የህዳሴዉን ገድብ ግንባታ ጨርሶ አግልግሎት የሚሰጥበት ደረጃ ላይ ለማድረስ ፕሮጀክቱ በዕቅድ ከተያዘለት በጀት ከሃምሳ በመቶ በላይ ሊያስፈልገዉ ይችላል። ይህ ደግሞ ዛሬ ወያኔን ስለምንቃወም የምናወራዉ ተራ የፕሮፓጋናዳ ጨዋታ ሳይሆን የዛሬ አራት አመት ወያኔ ከበቂ ጥናትና ዝግጅት ዉጭ አባይን እገድባለሁ ብሎ ሲፎክር የዛሬዋ ቀን እንደምትመጣ አዉቀን በተከታታይ ያስጠነቀቅነዉ ማስጠንቀቂያ ስለሆነ ነዉ። ይህ ሁሉ የሚያሳየን ወያኔ አስቀያሚ መልኩን ለማሳመር ሲል ብቻ በኢትዮጵያ ህዝብ ገንዘብና ጉልበት የህፃን ጨዋታ መጫወቱን ነዉ። ሆኖም ዛሬ የሚያስፈራን ይህ ወያኔ የተጫወተበት መጠነ ብዙ የህዝብ ገንዘብ ብቻ ሳይሆን ግድቡን ሰርቶ ለመጨረስ ተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘት የሚያደርገዉ አጉል መቅበዝበዝ ነዉ። በእኛ እምነት የህዳሴዉ ግደብ ተሰርቶ ሲያልቅ ኢትዮጵያን ከጥገኝነት ነፃ ማዉጣት ነዉ ያለበት እንጂ ሌላ አላስፈላጊ የሆነ የፖለቲካ ጥገኝነት ዉስጥ ይዞን መግባት የለበትም። ለዚህም ነዉ አርበኞች ግንቦት ሰባት ወያኔ፤ ግብፅና ሱዳን በአባይ ወንዛችን ላይ የሚሰራዉን ግድብ አስመልክቶ ደረሰን የሚሉትን ስምምነት ምኑም ሳይደበቅ ለኢትዮጵያ ህዝብ በግልጽ መነገር አለበት እያለ ህዝብንም ወያኔንም የሚያስጠነቅቀዉ። የግብፅና የሱዳን መንግስታት አገራቸዉ ዉስጥ ህዝብ የሚወዳቸዉ ወይም የሚጠላቸዉ መንግስታት ሊሆኑ ይችላሉ፤ ሆኖም ከዉጭ መንግስታት ጋር በሚያደርጉት ምንም አይነት ድርድርና ዉይይት ሽንጣቸዉን ገትረዉ የሚቆሙት ለአገራቸዉ ጥቅም ብቻ ነዉ እንጂ ሌላ ከህዝብና ከአገር የተለየ አጀንዳ የላቸዉም። ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉ አገዛዝ በተለይ ባለፉት ሃያ አራት አመታት ብቻዉን ስልጣን ተቆጣጥሮ የኖረዉ ህወሓት ግን ከኢትዮጵያ ህዝብ ዘለቄታዊ ጥቅም የተለየ የራሱ የሆነ አጀንዳ አለዉ። አርበኞች ግንባት 7 ህወሓትንና ይህንን ከህዝብና ከአገር የተለየ አጀንዳዉን የማቆሚያዉ ግዜ ዛሬ ነዉና ጉልበት ያለህ በጉልበትህ፤ ገንዘብ ያለህ በገንዘብህ፤ እዉቀት ያለህ ደገሞ በእዉቀትህ ነገ ሳይሆን ዛሬ ህዝባዊዉን ትግል ተቀላቀል እያለ አገራዊ ጥሪ ያስተላልፋል።

## ፊንጫ ስኳር ፋብሪካ ዉስጥ እሳት በሰዉና በንብረት

... ( ከገጽ 4 የዞረ )

እንዲያደርግም አሳስበዋል።

ከአዲስ አበባ በ350 ኪሎ ሜትር ርቀት በኦሮሚያ ክልል ፊንጫ ልዩ ስሙ ለምለም በረሃ በሚባለው ሥፍራ የሚገኘው ፊንጫ ስኳር ፋብሪካ፣ በደርግ ዘመን ግንባታው የተጀመረ ቢሆንም ማምረት የጀመረው በ1991 ዓ.ም. ነው። ፊንጫ ስኳር ፋብሪካ ከኅዳር ወር 2007 ዓ.ም. እስከ የካቲት ወር መጨረሻ ድረስ 87,710 ቶን ስኳር ያመረተ መሆኑን፣ መተሐራ ስኳር ፋብሪካ ከ58 ሺሕ ቶን በላይ፣ ወንጂ ስኳር ፋብሪካ ደግሞ ከ55 ሺሕ ቶን በላይ ስኳር ማምረታቸው ታውቋል። ለፋብሪካው 21,000 ሔክታር የሸንኮራ አገዳ መትከያ ማስፋፊያ ተደርጎለታል። ፋብሪካውም በተደረገለት የማስፋፊያ ሥራ የሸንኮራ አገዳ የመፍጨት አቅሙን ከ5,000 ቶን ወደ 12,000 ቶን አሳድጓል። በዓመት 270,000 ቶን ስኳርና 20,000 ሜትር ኩብ ኢታኖል እንደሚያመርትም ታውቋል።